ooooooooooooooooooooooooooooooooooooo

ቅዱስ አባ ጳላሞን ፈላሲ ባሕታዊ

ወቅዱስ አባ ጳላሞን ዐቢይ

[የአባ ጳኩሚስ መንፈሳዊ አባት]



ሐምሌ ፳፩ | ፳የ፲፫

በሕይወተ መነኮሳት ወመነኮሳይያት

|በፍሱሕ በፋሲካ|

ooooooooooooooooooooooooooooooooooooo

የጽሑፍ ማውጫ

1. ንስሐ ዘጰላሞን ፈላሲ ወባሕታዊ..... 3

2. ገድል ወጸጋ ጰላሞን ፈላሲ ወባሕታዊ..... 11

3. ሕይወተ አባ ጰላሞን ዐቢይ ድህረ ምጽአተ አባ ጳኩሚስ..... 12

ንስሐ ዘጰላሞን

በዚህች ቀን በ316 ዓ.ም አባ **ጰላሞን** ባሕታዊ አረፈ። በግብጽ በ**ቄና** ክፍለ ግዛት በ**ነጋአ-ሃምዲ** አውራጃ **ኤልከስሪ** እና **ኤልሳያድ** በሚባሉ ከተሞች ውስጥ ባለ ምስራቃዊው ተራራ ነበር የሚኖረው። ዲያብሎስ እርሱን ለመፈተን እስኪታክተው ድረስ ተጋደለ ፤ በአንዳችም አላሸነፈውም ነበር። ዲያብሎስ እያንዳንዱን አጋጣሚ ወጥመዱን ወደርሱ ለማምጣት ይጠቀም ነበር።

ከዕለታት በአንዱ ቀን **የእግዚአብሔር** ሰው አባ **ጰላሞን** የእጁን ስራ ይዞ ወደ ገጠራማው የግብጽ ክፍል ጉዞውን ጀመረ። በመንገድ እየሄደ ሳለ ስለ ኃጢአቶቹ ያለቅስ ነበር። የመልካም ነገር ጠላት አስቶት ለሰባት ቀናት በተራራው ውስጥ መራው፤ ወቅቱ በጋ ነበርና ከረሀብ እና ጥም የተነሳ ወደሞት እስኪቀርብ ድረስ ፈተነው። በመጨረሻም ዝሎ መሬት ላይ ወደቀ ሞቱንም ተመኘ።

የሰው ወዳጅ የሆነው **እግዚአብሔር** አገልጋዩን አባ **ጰላሞን** ለጠላት አሳልፎ አልሰጠውም፤ ሰይጣኑ እንዲተወው አዘዘው። አረጋዊው አባት ይህን የጌታ እርዳታ ባስተዋለ ጊዜ "*አ ጌታዬ* ***ኢየሱስ ክርስቶስ*** *ሆይ ፈርዳኝ*" ብሎ ጮኸ።

ወዲያው እንዲህ የሚል ድምጽ ሰማ "ጠላት ድል ኢይነሳህምና አትፍራ። ተነሳና ወደ ደቡብ አቅጣጫ አጭር ርቀት ተጓዝ፤ በዚያ **ታላሱን** የተባለ አረጋዊ መነኩሴ ታገኛለህ። ዲያብሎስ ያመጣብህን ነገር እና በወጣትነትህ የፈተነህን ክፉ ኃጢአት ሁሉ ንገረው። ኃጢአቶቹህ እንዲሰረዩ ሰላንተም ይጸልያል።"

❖ ቡሩክ አባ **ጸላሞን** የእጁን ስራ ይዞ መዝሙር **54**ትን እየጸለየ በተራራው ተጓዘ።

*"አቤቱ በሰምህ ኢድነኝ፤ በኃይልህም ፍረድልኝ አቤቱ ጸሎቴን ሰማ፤ የአፌንም ቃል ኢድምጥ። እንግዶች ቁመውብኛልና፤ ኃያላንም ነፍሴን ሸተዋታልና፣**እግዚአብሔርን** በፊታቸው አላደረጉትም፣እነሆ እኔ ግን **እግዚአብሔር** ይረዳኛል፣ጌታዬም ለነፍሴ ደጋፊዋ ነው። ክፋትን ወደ ጠላቶቼ ይመልሳታል፣ በእውነትህም አጥፋቸው። እነሆ እኔ ግን ከፈቃዴ እሰዋልሃለሁ፤ መልካም ነውና ሰምህን አመሰግናለሁ፤ከመከራ ኢድኖኛልና፤ አምድ በጠላቶቼ ላይ ኢይታለችና።"*

❖ ዳግመኛም መዝሙር **68**ትን እየደገመ ነበር፡-

*"**እግዚአብሔር** ይነሳ ጠላቶቹ ይበተኑ፣ የሚጠሉትም ከፊቱ ይሸሹ። ጢስ እንደሚበንን እንዲሁ ይብነኑ፤ ሰም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ፥ እንዲሁ ክፉዎች ከእግዚአብሔር ፊት ይጥፉ። ጻድቃንም ደስ ይበላቸው፥ በእግዚአብሔርም ፊት ሐሤት ያድርጉ፥ በደስታም ደስ ይበላቸው።.." እግዚአብሔር ወደ አባ ታላሱን ሰፍራ እሰኪያደርሰው ድረስ ጸሎቱን አላቋረጠም ነበር።*

አባ ታላሱን ባየው ጊዜ አብዝቶ ተደሰተ፤ ሰላምታ ከሰጠው በኃላ እጁን ይዞ እርሱ ወዳለበት ድንጋይ አወጣው። አብረው ከጸለዩ በኃላ ተቀምጠው ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት ማውራት ጀመሩ።

አባ ታላሱን አባ ጳላሞን ወደዚህ በረሃ ወደርሱ እንዴት እንደደረሰ ጠየቀው። አባ ጳላሞን ማንባት ጀመረ፤ በፊቱ ተንበርክኮም "ታውዳጅ ቅዱስ አባት ሆይ ይቅር በለኝ" አለው። አባ ታላሱን መልሶ "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሁላችንንም በደል ይቅር ይላል" አለው። አባ ፓላሞን እንዲህ አለው ፦

" ቅዱስ አባት ሆይ ባለማወቄ ከዲያብሎስ የደረሰብኝን ታላቅ ኃጢአት መናገር ያሳፍረኛል" አባ ታላሱንም መልሶ "እርሰ በርሳችሁ ኃጢአታችሁን ተናዘዙ፣ ትፈወሱ ዘንድ" ተብሎ ተጽፏል አለው።

አባ ጳላሞን የተባረከ አባት አባ ታላሱን የሚያጽናና እና የሚያበረታ አባት መሆኑን ሲያይ ይነግረው ጀመር።

በገዳም ስኖር **እግዚአብሔር** ኃጢአቶቼን ይቅር እንዲል እጠይቀው ነበር። በ**መንፈስ ቅዱስ** አነሳሽነት የተጻፉ **ቅዱሳት** መጻሕፍት ውስጥ የብሕትውና ሕይወት ፈሪሃ **እግዚአብሔርን** እንደሚያመጣ እና **እግዚአብሔር** ስላቅን እና በከንቱ መሳቅን እንደሚንቅ/እንደሚጠላ አነብ ነበር። ስለዚህ በትንሿ መኖሪያዬ የብሕትውና(ብቸኝነት) ሕይወት ለመኖር ወሰንኩ። ማንንም አለማውራት፣ በፍጹም በከንቱ አለመሳቅ ነገር ግን ስለኃጢአቶቼ መዓልት እና ሌሊት ማልቀስ ጀመርኩ።

ዲያብሎስ ዘውትር ይዋጋኝ ነበር። በሳቅ እና ስላቅ ልቤን ደስ ለማሰኘት ይሞክር ነበር፣ ነግር ግን እኔ ትኩረት አልሰጠሁትም፤ በፍጹም መልሼ እንኳ አልረገምኩትም። በነዚህ መከራዎች ለረዥም ጊዜያት ተጋደልኩ፥ ጠላት ቁጣው በኔ ላይ እስኪነድ ድረስ በ**ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ** ማዳን ጸናሁ።

ከዕለታት በአንዱ ቀን የእጄን ስራ ይዤ ለመሸጥ እና ትንሽ ዳቦ ለመግዛት በተራራው ተጓዝኩ። ከመኖሪያዬ ከራቅኩ በኃላ ዲያብሎስ ማረከኝ፣ ወዲያው አዕምሮዬን ሳትኩ። ከአንደበቴም **የእግዚአብሔርን** ስም ሰለበው፣ ጸሎትም አቋረጥኩ። ተራራው በጠቅላላ በፊቴ ተለውጦ የምድሩ አሸዋ ጥቁር ሆነ። በፊቴ ስመለከት አዲስ ከተማ አየሁ፥ በውስጧ የሚያማምሩ ሕንጻዎች፣ የተዋቡ ቤቶች፣ ውድ አብያተመንግስት እና እንደ ንጉስ ከተማ በአምባ ላይ የተሰራች፣ በዛፎች እና አጸዶች የተከበበች ከተማ አየሁ።

በአየሁ ጊዜ ስለከተማዋ ታላቅነት እጅግ አደነቅሁ። የከተማዋ ሰዎች የእጄን ስራ እንዲገዙኝ ወደከተማዋ ለመግባት ጀመርኩ። ወደ ከተማዋ ግንብ በቀረብኩ ጊዜ የጉድጓድ ውሃ እና ባጠገቡ አንዲት ያዘነች ሴት አየሁ። ፊቱ በጣም የጠቆረ ነበር። ልብሶቿ የተቀዳደዱ ነበር፣ በአይነርግብም አይኖቿን ሸፍና ነበር።

ከውሃው ጉድጓድ አጠገብ ቆማ ውሃውን በማውጣት አጸዶቹን ታጠጣ ነበር። ባየችኝ ጊዜ ተቀመጠች፣ ራሷንም ተከናንባ *"ቅዱስ አባት ሆይ ባርከኝ"* አለችኝ። በፍጥነት ቅርጫቶቹን ከፊቴ አስቀምጣ እንዲህ አለችኝ፡-*"ተወዳጅ አባት ሆይ ተቀመጥ፣ አረፍም በል ከሸክምህ የተነሳ ደክምሃልና"* ከጉድጓዱ ውሃ አጠገብ እንድቀመጥ ካረገችኝ በኃላ በእጆቿ ውሃ ወስዳ በረከት እንደሚቀበል ሰው እግሮቼን አጠበች። አኳኋኗም ሀብታም ባል እንዳላት ሴት ነበር።

እንዲህ ብዬ ጠየኳት፡- *"አንቺ የእምነት ሴት ሆይ ወደዚህ ከተማ ብገባ የእጆቼን ስራ የሚገዛኝ አገኝ ይሆን?"* እርሷም *"አዎን ይገዙሃል፣ ባይሆን እንኳ አታስብ እኔ እገዛሃለሁ፣ የምትፈልገውን ሁሉም እሰጥሃለሁ። እኔ በቅርቡ የሞተ የአንድ ባለጸጋ ሚስት ነኝ፤ ብዙ ገንዘብ እና ከብቶች ትቶልኝ ነው ያረፈው። የዚህን ሁሉ አዝመራ ፍሬም እሰበስባለሁ፥ የሚቆጣጠርልኝ ሰው የለኝም። ንብረቶቼን ሁሉ በአደራ የምሰጠው፣ ተገቢ ነው ባለው መንገድ የሚቆጣጠርልኝ እንዳንተ ኣይነት ሰው ባገኝ ብዬ እመኛለሁ። ቅዱስ አባት ሆይ ስለዚህ መጥተህ ቤቴን ለማስተዳደር እና ንብረቶቼን ለመቆጣጠር የምትቀበለኝ ከሆነ እንደ ባሌ ኣድርጌ ወስድሃለሁ"* አለችኝ።

❖ *መልሼ እንዲህ አልኳት፦-*

“መነኩሴ ካገባ እፍረት እና ውርደት ይከተለዋል።” ሴትዮዋም መልሳ *" እንደሚሰትህ የማትቀበለኝ ከሆነ ቢያንስ የንብረቶቼ ተቆጣጣሪ ሁን። ቀን ማሳዎችን፣ ከብቶችን፣ ጎተራዎችን፣ የወይን ሰፍራዎችን፣ ባሮችን እና አገልጋዮችን ትቆጣጠራለህ ማታ ሲመጣ ደግም ጸሎትህን መጸለይ ትችላለህ"።*

ከዚያን ተነስታ ወደቤቷ ወሰደችኝ። የተለያዩ አይነት ምግቦችን አዘጋጅታ በፊቴ አቀረበች። ከዚያ ወደ ክፍሏ ሄዳ እጅግ ወድ እና የቅንጦት ልብሶችን ለብሳ መጥታ አቀፈችኝ። ተገረምኩ እና **በእግዚአብሔር** ኃይል በመታመን በመስቀል ምልክት አማተብኩ። ያየሁት ነገር ሁሉ በነፋስ ፊት እንዳለ ጭስ ተሰወረ፤ ሴትዮዋ ያረገችው ነገር ሁሉ አልቀረም ነበር።

በዚያች ቅጽበት ይህ ሁሉ እኔን በኃጢአት ለመጣል የተመኘ ሰይጣን ስራ መሆኑን አወቅሁ። አምርሬ አለቀስኩ ባደረግሁት ነገርም እጅግ ተጸጸትኩ። **ጌታ**ም ራራልኝ የበዛ ምሕረቱንም በኔ ላይ አደረገ፣ **መልአኩን** ልኮ አጽናናኝ፣ ለኃጢአቴም ይቅርታ እንደማገኝ ቃል ገባልኝ፣ እንዲህም አለኝ፦- *"ወደ አንተ ቅርብ ወዳለው ወደ **ቅዱስ** አባ **ታላሱን** ሂድ፣ ኃጢትህንም ተናዘዝ። ጌታ በጸሎቱ እንዲምርህ ወደርሱ እንደመጣህ ንገረው"።*

አባ **ታላሱንም** እንዲህ እያለ ጸለየ፦ *"ልጄ ሆይ ጌታ አንተንም እኔንም ይቅር ይበለን"*። አስከትሎም ከሰማይ ማዕድ ወረደ አብረው ከተመገቡ በኃላ አባ **ጰላሞን** ወደ አምልኮ ስፍራው በሰላም ተመለሰ።

ገድል ወጺጋ ጰላሞን

ይህ **ቅዱስ** ከ**እግዚአብሔር** የመፈወስ ጸጋ ተሰጥቶት ነበር። የበረሃ አውሬዎችም ይወዳጁት ነበር፣ በእጆቹ ይመግባቸዋል፥ እግሩንም ይልሱ ነበር። ከልብስ ተራቁቶ ነበር የኖረው፣ በዚህም **እግዚአብሔር** ሰውነቱን እንዲሸፍንለት ጸጉሩን አስረዝሞት ነበር። ሳምንቱን ጾሞ ቅዳሜ እና እሁድ ነበር የሚመገበው። **እግዚአብሔር** በቁራ የሚልክለትን ግማሽ ዳቦ ይመገብ ነበር፤ ብዙ ጊዜ ከተራራው ሳር ይመገብ ነበር። ልክ እንደፈጣሪው መሐሪ፣ አዛኝ፣ እና ርህሩህ ነበር።

ሌሊት ሲመጣ ከአምልኮ ስፍራው ወርዶ እስረኞችን፣ ወላጅ አልባዎችን፣ ባል የሞተባቸውን(መበለቶችን)፣ በችግር ውስጥ ያሉትን፣ እና ተጓዦችን አቅሙ በፈቀደው ሁሉ ከእጁ ስራ በሚያገኘው ይረዳ ነበር። **ቅዱስ ጰላሞን** በተጋድሎው እና አምልኮው ቀናዒ ነበር። የሕይወቱን ሁሉንም ቀናት በቀን እና በሌሊት ጸሎት ይተጋ ነበር፣ እንዲሁም ሌሊቱን በንቃት እና ትግኃ ሌሊት ያሳልፍ ነበር።

ሕይወተ አባ ጳላሞን ዐቢይ ድህረ ምጽአተ አባ ጳኩሚስ

አባ ጳኩሚስ የምንኩስና አንድነት ሥርዓት መስራች አባት የዚህ አባት ደቀመዝሙር ነበር። ቅዱስ ጳኩሚስ ከአህዛብነት ወደ ክርስትና ሲመጣ የአምልኮ እና የትሕርምት ሕይወትን መኖር ይሻ ነበር፤ ስለዚህም የመኖሪያ ከተማው ካህን ወደ ታላቁ ባሕታዊ ወደ አባ ጳላሞን መራው።

ጳኩሚስም በከተማው ያሉትን ድኾች እና ችግረኞች እንክብካቤ ለአንድ አረጋዊ መነኩሴ አደራ ሰጥቶ ወደ አባ ጳላሞን ሄደ። በደረሰ ጊዜ የበዓቱን በር አንኳኳ፤ አረጋዊው አባትም በቀዳዳ ተመልክቶ *"ወንድሜ ሆይ አንተ ማነህ?" "ምን ትሻለህ?"* አለው። ጳኩሚስ ፈጥኖ እንዲህ አለ፦ *" እኔ አንተ የምታመልከውን እግዚአብሔር የሆነውን ክርስቶስ የምሻ ነኝ፣ አንተ በአባትነት እንድትቀበለኝ እና እንድታመነኩሰኝ እማጸንሃለሁ።"*

አባ ጳላሞን መልሶ *"ልጄ ሆይ ምንኩሰና ያልተገደበ ትግል/ተጋድሎ ኣይደለም፤ ሰውም እንዳሻው የሚገባበት ኣይደለም፤ ብዙዎች ክብደቱን ሳይረዱ ገብተውበት መቋቋም ተሰናኣቸዋልና። አንተም የሰማኸው ተጋድሎውን ሳታውቅ ነው።"*

ጳኩሚስም መልሶ *"ጥያቄዬን እና መሻቴን ኣታሳፍረኝ፣ የቅንዓቴን እሳትም ኣታጥፋው፤ ተቀበለኝ፣ ታገሰኝና ፈትነኝ ከዚያን ይገባል የምትለውን ኣድርግ።"* አረጋዊውም አለው "ልጄ ሄድ እና ራስህን ለተወሰነ ጊዜ ለብቻ መርምር ከዚያን ተመልሰህ ወደኔ ና፤ እኔ ድካሜ በፈቀደ ሁሉ ራስህን እንድታወቅ ከአንተ ጋር ለመስራት ፈቃደኛ ነኝ። የምንኩስና ጽድቅ ብርታትን እን ትሕርምትን ይፈልጋል እኔም የመጀመሪያውን ደረጃ አስተምርሃለሁ። ከዚያን ሄደህ እንደምትሸከመው ወይም እንደሚያቅትህ ራስህን ትመረምራለህ። ዓላማዬም ለሌላ ምክንያት ሳይሆን አንተን ለማስተማር እንደሆነ **እግዚአብሔር** ያውቃል።

ተወዳጅ ልጄ ሆይ የዚህን አለም ከንቱነት እና ማታለል ስናውቅ ወደዚህ ወደ ሩቅ ቦታ መጣን። በትከሻችንም **የጌታችንን መስቀል** ተሸከምን፤ **ዕጸ መስቀሉን** ሳይሆን ነገር ግን ስጋን ማሸነፍ፣ፍትወታቱንም ማስገዛት እና ኃይሉን ማባከን ነው(የስጋን) ነው እንጂ። ሌሊቱን በጸሎት እና **እግዚአብሔርን** በማመስገን እናሳልፋለን። ዘውትር ከፀሐይ መግባት አንስቶ እስከ ንጋት/ጠዋት ድረስ በጸሎት እና በእጃችን ብዙ በመስራት፤ ወይ ገመድ መስራት፣ ሰሌን መታታት፣ ቁርበት በመስራት ወይም ልጥ በመጥለፍ እንቅልፍን እንቋቋማለን። ለሰውነታችን የሚያስፈልገውንም ሆነ ችጋረኛ የምንመግብበት እናገኛለን። **ሐዋሪያውም** እንዲህ እንዳለ:- ***" ችጋረኛውን ኣትርሱት"።***

በጠቅላላው ዘይት መመገብን አናውቅም፣ የበሰለ ምግብም ሆነ የሚያስክር መጠጥ እንዲሁ። በበጋ ወቅት እስከ ምሽት እንጾማለን፥ በክረምት ደግሞ ሁለት ቀን ከጾምን በኃላ በሕብስት እና ጨው ጾም እንፈታለን። ድብርትን/መታከትን ሞትን በማስታወስ(ተዘክሮ ሞት) እና ምን ያህል የቀረበ እንደሆነ በማስታወስ እናርቃለን።

የትኛውንም ክብር(ትዕቢት) እና ከፍታ እንቃወማለን፤ ራሳችንንም ከክፉ ሀሳቦች በትህትና እና ጽድቅ እንጠብቃለን። በዚህም **በእግዚአብሔር** ጸጋ በሚፈጸም ትሕርምታዊ ተጋድሎ ነፍሶቻችንን **ለእግዚአብሔር** ደስ የሚያሰኝ ሕያው መስዋዕት አድርገን እናቀርባለን።ይህም አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ብዙ ጊዜ ነው። በዚህም ተጋድሎ እና በምንተጋው ትጋት መጠን መንፈሳዊ ስጦታዎችን እናስተውላለን። **የጌታንም** ቃል እያስታወስን እንዲህ የሚለውን፡- ***"ትዕግሰትን የሚያበዙ ነፍሳቸውን ያድናሉ"***

ጳኩሚስ ከአባ **ጳላሞን** ሰምቶ የማያውቃቸውን እንዚህን ነገሮች ሲሰማ በመንፈሱ ፤ እርግጠኛ ሆነ፤ ክብደቱን እና ሕማሙን የሚጋፈጥበትን ብርታት አገኘ። መልሶም እንዲህ አለ፡- *"ጌታዬ **ኢየሱስ ክርስቶስ** እታመናለሁ በመቀጠልም ባንተ ጸሎት፤ በዚህም እነዚህን ቅደመሁኔታዎች መከወን ይቻለኛል፥ እስከምትም ድረስ ካንተ ጋር እተጋለሁ"* አለ። በፊቱም ተንበርክኮ እጁን ሳመው። አረጋዊውም የስጋን ፈቃድ ስለመግደል፣ ስለ ትህና እና የተሰበረ ልብ ሰበከው፣ አስተማረው።

"የነገርኩህን ከጠበቅህ እና ወደኃላ ካልተመለስክ ወይም በሁለት ሀሳቦች መሀል ካልወላወልክ እኛ ባንተ ጋር እንደሰታለን" ቀጥሎም እንዲህ አለው፡- *"ልጄ ስለተጋድሎ፣ ጸሎት፣ ትጋት፣ ጾም በነገርኩህ ነገር ሁሉ ከሰዎች ክብርን የምንጠይቅ ይመስልሃል? አይደለም ልጄ እንደዚያ አይደለም። ነገር ግን ወደ ድኅነት ሰራዎች እንመራሃለን፤ ይህም ከነቀፋ እንድንድን ነው፥ እንዲህ ተብሎ ተጽፏልና፡-* ***"የተከደነ ያልተገለጠ ነገር የለም"*** *እና* ***"በብዙ መከራ ወደ መንግስተ ሰማይ እንገባ ዘንድ ይገባል"።***

አሁን ወደ መኖሪያህ ሂድ፥ ራስህን መመርመር እንድትችል። የጠየከውም ነገር ቀላል አለመሆኑን ራስህን ፈትን። **ጳኩሚስም** መልሶ *"በሁሉ ነገር ራሴን መርምርያለሁ፥* **በእግዚአብሔር** *ጸጋ እና* **ቅድስት** *ጸሎትህን ልብህ ደስ እንደሚሰኝብኝ ተሰፋ አደርጋለሁ"* አረጋዊው አባትም መልሶ ***"መልካም"*** አለው።

አባ **ጳላሞን** በደስታ ተቀበለው፤ በጸሎት፣ ትጋት እና ጾም እስከ 10ቀን እየፈተነው ቆየ። ከሦስት ወራት በኃላ ትዕግስቱን ፣ጽናቱን፣ ጥረቱን እና ፈቃዱን ከፈተነ በኃላ በርሱ ላይ ጸልዮ ጸጉሩን ቆረጠ ከዚያንም የመነኮሳትን ልብስ(አስኬማ) አለበሰው። ይህም በ304 ዓም ነው።

አብረው በተጋድሎ እና ጸሎት መትጋት ጀመሩ። በትርፍ ሰዓታቸው ቁርበት መስራት እና ልብስ በመጥለፍ በሚያገኙት ጥቂት የሚያስፈልጋቸውን በማሟላት እና ከተረፈችው ለችጋረኛ መስጠት ቀጠሉ። በትግኃ ሌሊት ሳሉ እንቅልፍ ከመጣባቸው ከበዓታቸው ይወጡ እና አሸዋ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ያጓጉዙ ነበር፤ ይህም ስጋቸውን ለማድከም እና እንቅልፍን ለማስወገድ ነው።

አረጋዊው አባት ወጣቱን ይመክረው እና ያበረታው ነበር።

"*ጳኩሚስ ሆይ በርታ፥ ለእግዚአብሔር አምላክ ያለህ አምልኮ በፍቅር እሳት የነደደ ይሁን፥ በፊቱም በፍርሃት፣ በትህትና እና በጸሎት በመትጋት እና ሳይታክቱ በመሰገድ ይሁን። ንቁ ሁን ያለበለዚያ ፈታኝ ይመረምርህ እና ያሳዝንሃል።*"

❖ በኤልባራሙስ ገዳም በአባ ጳኩሚስ ገድል የሚከተለው ሰፍሯል:

ከዕለታት በአንዱ ቀን የሆነ ሰው ይጎበኛቸው እና ሌሊቱን ከነርሱ ጋር ያሳልፍ ዘንድ የቅዱሳኑን አባ ጳላሞን እና ጳኩሚስ በዓት በር አንኳኳ። ትዕቢት እና በራስ መመካት ድል የነሱት ሰው ነበር።

ስለ እግዚአብሔር ቃል ቁጭ ብለው እያወሩ ነበር፥ ወቅቱ ክረምት ነበርና በፊታቸው እሳት እየነደደ ነበር። እንግዳው ሰው እንዲህ አላቸው፡- "*ከናንተ መሃል በእግዚአብሔር ላይ ጠንካራ እምነት ያለው ማነው፥ አሁን ይነሳና በግለቱ ፍም ላይ ቆሞ ጌታ ለደቀመዛሙርቱ ያስተማረውን ጸሎት ይድገም*"።

አረጋዊው አባት አባ **ጳላሞን** ይህን ሲሰማ እንዲህ እያለ ገሰጸው፡- *"ይህንን ክፉ ሀሳብ በልብህ የተከለ ዲያብሎስ የተረገመ ነው። ስለዚህ ንግግርህን አቁም።"* እንግዳው ግን የአረጋዊውን ቃላት ትኩረት አልሰጣቸውም እንዲህ አለ *"እኔ ራሴ አደርገዋለሁ"።* ተነስቶ በጋለው ፍም ላይ ቆመ፥ ቀስ ብሎም **አቡነ ዘበሰማያት**ን ደገመ። ከዚያን ሰውነቱን አንዳች ያልጎዳውን እሳት ላይ ተረማምዶ በግብዝነት ወደ መኖሪያው ሄደ።

ጳኩሚስ ለአባ **ጳላሞን** እንዲህ አለው፡- " *ስለዚህ የእሳት ግለት ላይ ስለቆመው እና እግሩ ስላልተቃጠለ ወንድም እንዳደነቅሁ* **እግዚአብሔር** *ያውቃል"።* አረጋዊው አባት መልሶ *"በዚህ አትደነቅ፥ ይህ ከሰይጣን መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።* **ጌታ** *እግሩ እንዳይቃጠል ያረገው እንዲህ ተብሎ ስለተጻፈ ነው፡-* ***"እግዚአብሔር ለጠማማው ጠማማ መንገድን ይልክለታል"።*** *ልጄ ሆይ እመነኝ በርሱ የተዘጋጀውን መከራ ብታውቅ ኖሮ ስለ ጉስቁልናው ታለቅስ ነበር።"*

ሰይጣን ወደዚህ ሰው በሴት አምሳል መጥቶ ወደ በዓቱ መግባት እንዲፈቅድላት አድርጎ አታለለው። ስለ ትዕቢቱ እና ስለ ልቦናው መታወር የከበበውን አደጋ አልተረዳም ነበር። ልቡ በርሷ ላይ በፍትወት ተሞላ፤ ወዲያው ዲያብሎስ መትቶ መሬት ላይ ጣለው፥ ለአንድ ቀንም እንደሞተ ሰው ሆነ። ወደ ልቦናው ሲመለስ እና አቅም ሲያገኝ ወደ **ጳላሞን** ስላደረገው ነገር እያለቀሰ እና እየተጸጸተ ሄደ።

እርዳታቸውን እና ጸሎታቸውንም ተማጸነ፤ ዲያብሎስ ከራሱ(ሰውዬው) ፈቃድ የተነሳ በባርነት ይዞታልና። ሲያወራቸው አረጋዊው አባት አባ ጳላሞን እና ደቀመዝሙሩ እያዘኑ ነበር፤ በድንገትም ክፉ መንፈስ መጣበት። ወደ ተራራው ሄደ፥ አዕምሮውን አጥቶ ነበር። ለተወሰነ ጊዜ ከጠፉ በኃላ እሳት ውስጥ ራሱን ወርውሮ ሞተ።

አረጋዊው አባት አባ ጳላሞን የተከሰተውን ሲያውቅ መሪር ሀዘን አዘነ። ደቀመዝሙሩም ጠየቀው እንዲህም አለው፡- " እግዚአብሔር እንዴት ይህ እንዲሆን ፈቀደ፣ ከተናዘዘና በዕንባና ጸጸት ንስሐን ከጠየቀ በኃላ ይህ እንዴት ሆነ?"

አባ ጳላሞንም መልሶ "የዚህ ወንድም ንስሐ ከልብ የሆነ እንዳልሆነ እግዚአብሔር ያውቃልና ስለዚህ የዘራውን እንዲያጭድ ተወው"።

ቅዱስ ጳኩሚስ ከመምህሩ ከአባ ጳላሞን ጋር እያለ ከዕለታት በአንዱ ቀን በበረሃው እየሄደ ታባንሲን ወደምትባል መንደር ሄደ። እየጸለየ ሳለ የጌታ መልአክ ተገለጠለት እና እንዲህ አለው፡- " ጳኩሚስ ሆይ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ መሠረት የቆምክባት ቦታ ላይ ገዳም ሰራ፥ ስለዚህ ብዙዎች ምንኩሰናን ሸተው ወዳንተ ይመጣሉ። " ወደ አረጋዊው አባት አባ ጳላሞን ተመልሶ የጌታ መልአክ የነገረውን እና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ያለውን ሀሳብ ነገረው።

አባ ጳላሞን በደቀመዝሙሩ መለየት አዝኖ ነበር፥ እንዲህም አለው "እንዴት ከሰባት አመታት የመታዘዝ እና መገዛት ሕይወት በኃላ ትተኸኝ ትሄዳለህ፣ እኔም ደግሞ አርጅቻለው። ትተኸኝ ከምትሄድ አብሬክ ብሄድ ቀላል ይሆናል።"

በደቡብ አቅጣጫ ተጉዘው ወደ ታባንሲን መጡ፤ በዚያም ገዳም መገንባት ጀመሩ። ይህም በ311 ዓም ነው። ጳኩሚስ 30 ዓመቱ ነበር፤ ገዳሙን ገንብተው በጨረሱ ጊዜ አባ ጳላሞን ለደቀመዝሙሩ ጳኩሚስ እንዲህ አለው ፦

"ተወዳጅ ልጄ ወደ በዓቴ እና ወደ ብሕትውና ሰፍራዬ ለመመለስ እናፍቃለሁ፤ አሁን እግዚአብሔር አንተ ይህን ገዳም እንድትመሠርት እንደመረጠ አውቄያለሁ፤ ይህም ገዳም የሚያድግ እና እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኙ መነኮሳት የተሞላ ይሆናል። መነኮሳቱን የምትመራበት ኃይልን እና ትዕግስት ትቀበላለህ። በኔ በኩል ደግሞ ያረጀሁ፣ የደከምኩ እና ዕለት ዕረፍቴም የቀረበ ሆኛለሁ። ስለዚህ የብሕትውና(ብቸኝነት) ሕይወቴ ለኔ የተሻለ ነው። ቢሆንም ግን በየጊዜው አንተን ማየትን እንዳትከለክለኝ እጠይቅሀለሁ። ባገኘኋቸው ጥቂት ቀናት እየመጣሁ እጎበኝሀለሁ።"

አብረው ከጸለዩ በኃላ ተለያዩ፤ አንዳቸው አንዳቸውን በየጊዜው ይጎበኙ ነበር።

እረፍቱ ለጸላሞን ዐቢይ

በአንዱ የአባ ጸላሞን ጉብኝት አባ ጸላሞን ታመመ፣ ከልጅነቱ ጀምሮ ይወደው እና ያገለግለው ወደ ነበረው ጌታ ሄደ። አባ ጳኩሚስ የመምህሩን በረከት ከተቀበለ በኃላ ገንዘ ቀበረው። ብዙ ድንቆች እና ተአምሮች በዚህ ቅዱስ ተከናወኑ።

ገዳሙ ለአባ ጸላሞን

በስሙ የተሰየመ ጥንታዊ ቤተክርስቲያን በኤልካስሪ እና ኤልሳያድ ከተማ በስሙ ባለ ገዳም ውስጥ ይገኛል። በገዳሙም ሌሎች በድንግል ማርያም፣ በቅዱስ ሚካኤል፣ በቅዱስ መርቆሪዎስ(አቡሰይፊን) እና ቅድስት ዴሚያና ስም የተሰየሙ አብያተክርስቲያናት ይገኛሉ። በዕለተ ዕረፍቱም ታላቅ በዓል ይደረጋል።

ጸሎቱ ከኛ ጋር ትሁን፥ ለእግዚአብሔርም ምስጋና ይሁን ለዘላለሙ አሜን።